# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

## ሁለተኛ ክፍል



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች
ማደራጃ መምሪያ ዓለም አቀፍ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ
# ሁለተኛ ክፍል

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች
ማደራጃ መምሪያ የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት
ት/ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ 2015 ዓ.ም

# መክሥተ አርእስት


| | |
|---|---|
| መግቢያ | |
| ምዕራፍ አንድ ፡ ደብተራ ኦሪት | ፩ |
| ምዕራፍ ሁለት ፡ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ (ምኵራብ) | ፫ |
| ምዕራፍ ሦስት ፡ የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን | ፫ |
| ምዕራፍ አራት ፡ የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ክፍሎች | ፯ |
| ፬.፩ ቅኔ ማኅሌት | ፰ |
| ፬.፪ ቅድስት | ፱ |
| ፬.፫ መቅደስ (ቅድስተ ቅዱሳን) | ፲፩ |
| የምዕራፉ ማጠቃለያ | ፲፩ |
| የማጠቃለያ መልመጃ | ፲፫ |

# ምዕራፍ አንድ
# ደብተራ ኦሪት

## የምዕራፉ ዓላማ
**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ**

- ስለ ደብተራ ኦሪት ምንነት ይረዳሉ፡፡

## ማስጀመሪያ ጥያቄዎች
ደብተራ ኦሪት ምን ማለት ነው

ሙሴ ከእናቱ ዮካብድ እና ከአባቱ እንበረም እስራኤላዊ ከሆኑ ቤተሰቦቹ በግብጽ ሀገር ተወለደ፡፡ እናቱም የአባቶቹን አምላክ ፈጣሪነቱን እንዲያውቅ ከልጅነት እድሜው ጀምራ ኮትኩታ አሳደገችው፤ ሙሴም በፈርዖን ቤት ለአርባ ዓመት ቆየ፡፡ ወገኖቹን እስራኤላውያንን ነፃ ያወጣ ዘንድ በሰማንያ ዓመቱ በደብረ-ሲና ተጠራ፡፡ በመልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ረዳትነት በእግዚአብሔር ፈቃድ ባህረ-ኤርትራን ከፍሎ ሕዝበ እስራኤልን አሻገረ፡፡

ሙሴ በደብረ ሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር በድጋሚ ተገለጠለት ታቦተ ጽዮንንም ሰጠው፡ ሕዝበ እስራኤልም መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን በታቦተ ጽዮን ፊት ይፈፅሙ ነበር፡፡ ሙሴ ለታቦተ ጽዮን ማረፊያ ይሆን ዘንድ ደብተራ ኦሪትን በቀይ፣ በሐምራዊ እና በሰማያዊ መጋረጃ አስውቦ ድንኳን ሠራ ይህን ድንኳን በሦስት ክፍል በመጋረጃ ከፋፈለው፡፡ አንዱንም ቅድስተ ቅዱሳን አለው፣ በውስጡም የቃል ኪዳኑን ታቦት አኖረው፡፡ ሁለተኛውን ክፍል ቅድስት አለው፤ በውስጡም ንዋየ-ቅዱሳትን አኖረ፡፡ እግዚአብሔርም በደመና አምሳል እየተገለፀ በዚህ የድንኳን ቤተ መቅደስ (ደብተራ ኦሪት) ሙሴን እና ሕዝበ እስራኤልን ያነጋግራቸው ነበር፣ እንዲሁም ይገስጻቸው ነበር፡፡ እስራኤላውያን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሲዘዋወሩ ደብተራ ኦሪትን ከተተከለችበት ነቅለው ይዘዋት ይዘዋወሩ ነበር፣ በአረፉበትም ስፍራ እንዲሁ ተክለው ሥርዓተ-አምልኳቸውን ያከናውናሉ፡፡ በዚህ የቤተ መቅደስ አገልግሎት ውስጥ ዋነኛ ተሳታፊ ነገደ ሌዊ ነበሩ፡፡



ሥዕል ፩ ፡ ደብተራ ኦሪት

# ምዕራፍ ሁለት
# የሰሎሞን ቤተ መቅደስ

## የምዕራፉ ዓላማ
### ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ

- ቅዱስ ሰሎሞን ስላሰራው ታላቁ ቤተመቅደስ ይረዳሉ።

## ማስጀመሪያ ጥያቄዎች
ታላቁን ቤተመቅደስ ማን ሰራው

ጠቢቡ ሰሎሞን ከአባቱ ከንጉሥ ዳዊት እና ከእናቱ ከቤርሳቤህ በእስራኤል ሀገር ተወለደ። ከአባቱ ዘንድ በመንፈሳዊ እና በአስተዳደር ትምህርት ተኮትኩቶ ያደገ ሲሆን በእግዚአብሔር ፊትም በጥበብ እና በሞገስ አደገ። አባቱ ንጉሥ ዳዊትም ጠቢቡ ሰሎሞንን በልጅነት እድሜው በእስራኤል ላይ አነገሠው። ንጉሥ ዳዊት ለታቦተ ጽዮን እጅግ ያማረ ቤተ መቅደስ መሥራት ይፈልግ ነበረ። ነገር ግን ይህንን ሳያደርግ አረፈ። ልጁ ጠቢቡ ሰሎሞን በእግዚአብሔር ፊት ጸለየ፣ እግዚአብሔርም "ምን እንዳደርግልህ ትሻለህ" ባለው ጊዜ፣ ጠቢቡ ሰሎሞን ሲመልስ "ሕዝብህን የምመራበት ማስተዋልና ጥበብ ስጠኝ" አለው። እግዚአብሔርም የልቡን መሻት ፈፀመለት፤ በምድር ላይም ጥበበኛ አደረገው። እግዚአብሔር በሰጠው ጥበብ እና ማስተዋል ተጠቅሞ እጅግ ውድ ከሆኑ እንጨቶች፣ የከበሩ ድንጋዮች፣ ወርቅ እና አልማዝ ተጠቅሞ ያማረውን ቤተ መቅደስ ሠራ። ቤተ-መቅደሱም አራት ማዕዘን የሆነ ነው። የቤተ-መቅደሱንም ግድግዳ፣ መስኮት እና መጋረጃ በቅዱሳን መላእክትና የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት የሚገልፁ ሥዕላትን በመሳል አስጌጠ፤ አጸደ ቤተ መቅደሱንም በተለያዩ ዕፅዋት እና አትክልት አስዋበ፣ እግዚአብሔርም ሰሎሞንን "ይህችን ስፍራ እንደ ዐይኔ ብሌን እጠብቃታለሁ" ብሎ ቃል ኪዳን ገባለት።



ሥዕል ፬ ፡ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ

# ምዕራፍ ሦስት
# የፊልጵስዩስ ቤተ-ክርስቲያን

## የምዕራፉ ዓላማ
**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ**

- ስለ መጀመሪያዋ የሐዲስ ኪዳን ሕንጻ ቤተክርስቲያን ያውቃሉ፡፡

## ማስጀመሪያ ጥያቄዎች
የመጀመሪያዋ የሐዲስ ኪዳን ሕንጻ ቤተክርስቲያን በየት ተሰራች

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፣ ቅዱሳን ሐዋርያት ባለሚሎቹ በፆም እና በጸሎት ሆነው ወደ እርሱ በለመኑ ጊዜ የልቦናቸውን መሻት ለመፈፀም ሰኔ ፳ ቀን ሐዋርያትን ከየሀገረ ስብከታቸው ሰበሰባቸው፡፡ የተሰበሰቡባትም ሀገር ፊልጵስዩስ ትባላለች፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከሦስት ድንጋዮች ቤተ መቅደስን በተአምራት ሠርቶ በአስፈላጊ ንዋየ ቅድሳት አሟልቶ ፣ ታቦተ ማርያምን አስገብቶ የቤተ-መቅደስ ሥራውን በመፈጸም በሰኔ ፳፩ ቀን የፊልጵስዩስ ቤተ-ክርስቲያንን አከበራት፤ ሐዋርያቱንም ቀድሶ አቆረባቸው ፤ በዚህ መሠረት ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በዓለም ዙሪያ ታነፁ፡፡ (ሰኔ ፳ ስንክሳር)

## መልመጃ
### ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ጻፉ!

፩. ደብተራ ኦሪትን የሠራው ማን ነው?
፪. የሙሴ እናት እና አባት ማን ተብለው ይጠራሉ?
፫. ምኩራብን የሠራው ጠቢቡ የእግዚአብሔር ባለሟል ማን ነው?
፬ ጠቢቡ ሰሎሞን ወደ እግዚአብሔር ምን ብሎ ጸለየ?
፭ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያነጻት ቤተክርስቲያን በየት ትገኛለች?



ከላይ የተሰጠውን ስዕል ቀለም በመጠቀም አቅልሙ!

# ምዕራፍ አራት
# የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ክፍሎች

## የምዕራፉ ግብ

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ**

- የቤተ ክርስቲያንን ክፍሎች ይዘረዝራሉ ፤
- በቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስትና መቅደስ ምን ዓይነት ሥርዓት እንደሚከናወን ይገልጻሉ።

## የተግባር ልምምድ

ልጆች ወደ ቤተ ክርስቲያን ግቡና በቅኔ ማኅሌት ውስጥ የሚገኙ ንዋያተ ቅዱሳትን ተመልክታችሁ ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው።

ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስንገባ በቅደም ተከተል ሦስት ክፍሎችን እናገኛለን። እነዚህ ሦስት ክፍሎች በግድግዳ ወይም በመጋረጃ የተከፋፈሉ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሦስት ክፍሎች የተለያየ ስያሜና አገልግሎት አላቸው።

ልጆች እነዚህን የቤተ ክርስቲያን ክፍሎች ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

## ፬. ፩ ቅኔ ማኅሌት

ይህ ክፍል ከውጭ ወደ ውስጥ ስንገባ መጀመሪያ ላይ የምናገኘው ክፍል ነው። ስያሜውን ያገኘው ከሚከናወንበት አገልግሎት ነው። መዘምራን፣ ካህናት፣ ደባትር ስብሐተ እግዚአብሔር፣ ማኅሌተ እግዚአብሔር የሚያደርሱበት፤ መዝሙር የሚዘምሩበት ቦታ ነው። በዚህ ክፍል ሊቃውንት ቅኔ ይቀኙበታል።

ይህ ክፍል ለቊርባን ያልበቁ ምእመናን ቆመው የሚያስቀድሱበት ክፍል ነው። በምሥራቅ፣ በሰሜንና በደቡብ በኩል ሦስት በሮች አሉት።




ሥዕል ፫ ፡ ቅኔ ማኅሌት



ሥዕል ፬ ፡ ካህናት፣መዘምራን በቅኔ ማኅሌት በዝማሬ አገልግሎት ላይ ሳሉ

## ፬. ፪ ቅድስት




ሥዕል ፭ ፡ ቅድስት

‹‹ቅድስት›› የሚለው ቃል ቀጥተኛ ፍቺ/ትርጉም ‹‹የተለየ ወይም ልዩ›› ማለት ሲሆን በቤተ መቅደሱ በሁለተኛ ደረጃ የሚገኝ ክፍል ነው፡፡ ይህ ክፍል ካህናት ለምእመናን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የሚያቀብሉበት፤ ለሙሽሮች ጸሎት የሚደርስበትና በካህናት እጅ የሚባረኩበት፣ የሚቆርቡ ምእመናን ቆመው የሚያስቀድሱበት ክፍል ነው፡፡

በቅድስት ውስጥ የማይቆርቡ ምእመናን ቆመው ማስቀደስ አይችሉም፡፡ ቅድስት በምሥራቅ፣ በምዕራብ፣ በሰሜንና በደቡብ አቅጣጫዎች አራት በሮች የሚኖሩት የቤተ መቅደስ ክፍል ነው፡፡



ሥዕል ፮ ፡ በቅድስት ካህናት ቅዱስ ቁርባንን ሲያቀብሉ

## ፬. ፫ መቅደስ

ይህ ክፍል የቤተ ክርስቲያኑ ማዕከላዊ ክፍል ነው። ይህ ክፍል የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚቀመጥበት ክፍል ነው። ቅድስተ ቅዱሳን በሚል ስያሜም ይታውቃል። ከመንበረ ታቦቱ በተጨማሪ ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት ይቀመጡበታል።




ሥዕል ፯ ፡ መቅደስ

ወደዚህ ክፍል ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ሰዎች ብቻ ነው መግባት የሚችሉት። በዚህ ክፍል ጳጳሳት የሚያስቀድሱበትና የጌታችን ሥጋና ደም የሚፈተትበት ክፍል ነው።

በምዕራብ፣ በሰሜንና በደቡብ በኩል ሦስት በሮች ያሉት ሲሆን በሮቹ መጋረጃዎች/ መንጦላዕት ይኖራቸዋል።

**የተግባር ልምምድ**

ልጆች በቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስትና መቅደስ ውስጥ ምን ዓይነት ሥርዓት እንደሚከናወን ካህናት አባቶችን ጠይቃችሁ በመምጣት ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

# የጨዋታ ሰንጠረዥ

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ሰንጠረዥ በተገቢው ቃላት አግድም እና ቁልቁል በተሰጣችሁ ፍንጭ መሠረት ሙሉ።

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | ፪ ደ | | | | ና | |
| | | | | | | | | | | | | | ፲ አ |
| ፩ ታ | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | ፫ | | ራ | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | ፬ መ | | | | | | | | |
| | | | | | ፭ | | | ት | | | | | |
| | | | ፮ | | | | | | | | | | ፲፩ |
| | | | | | ስ | | | | | | ፱ | | |
| | | | | | | | | | | | ካ | | |
| | | | ፯ ስ | | ፰ | | | | | | | | |
| ፲፪ | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | ያ | | | | | | | | |
| ፲፫ ቅ | | | | | | | ፲፬ | | | | | | ን |

## ቁልቁል

፩ በማዕከላዊው የቤተ ክርስቲያን ክፍል በመቅደስ ውስጥ የሚገኝ
፪ ለታቦተ ጽዮን ማረፊያ ይሆን ዘንድ የተሠራ የድንኳን መቅደስ
፬ ካህናት አባቶች ብቻ የሚገቡበት የቤተ መቅደስ ክፍል
፮ ጌታችን በተዓምራት በሦስት ድንጋይ ቤተ ክርስቲያን የሰራባት ሀገር
፰ የጌታችን ባለሟሎች በጾም እና በጸሎት ሆነው ወደ እርሱ ይጸልዩ የነበሩ
፱ የሙሴ እናት ስም
፲ የሙሴ አባት ስም
፲፩ ክርስቲያኖች ተሰብስበው የሚጸልዩባት ፣ የሚቆርቡባት ፣ የሚማሩባት የተቀደሰች ስፍራ
፲፪ ወደ ቅኔ ማኅሌት ካህናት አባቶች የሚገቡበት በር ያለበት አቅጣጫ

## አግድም

፪ ሙሴ ከእግዚአብሔር ታቦተ ጽዮንን የተቀበለበት ተራራ
፫ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ
፭ ምዕመናን ቅዱስ ቁርባን የሚቀበሉበት የቤተ መቅደስ ክፍል
፯ ካህናት አባቶች ለእግዚአብሔር በቅኔ ማኅሌት የሚያቀርቡት ምስጋና
፲፫ ካህናት አባቶች ምስጋና የሚያቀርቡበት የመቅደስ ክፍል
፲፬ ምኩራብን የሠራው ጠቢብ

## የጨዋታ ሰንጠረዥ ቁልፍ

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | ፪ ደ | ብ | ረ | ሲ | ና | |
| | | | | | | | | ብ | | | | | ፲ እ |
| ፩ ታ | | | | | | | | ተ | | | | | ን |
| ቦ | | | | | | ፫ ም | ኩ | ራ | ብ | | | | በ |
| ት | | | | | | | | አ | | | | | ረ |
| | | | | | ፬ መ | | | ሪ | | | | | ም |
| | | | | | ፭ ቅ | ድ | ስ | ት | | | | | |
| | | | ፮ ፊ | | ደ | | | | | | | | ፲፩ ቤ |
| | | | ል | | ስ | | | | | | ፱ ዮ | | ተ |
| | | | ጵ | | | | | | | | ካ | | ክ |
| | | | ፯ ስ | ብ | ፰ ሐ | ተ | እ | ግ | ዚ | አ | ብ | ሔ | ር |
| ፲፪ ም | | | ዩ | | ዋ | | | | | | ድ | | ስ |
| ሥ | | | ስ | | ር | | | | | | | | ቲ |
| ራ | | | | | ያ | | | | | | | | ያ |
| ፲፫ ቅ | ኔ | ማ | ጎ | ሌ | ት | | ፲፬ ጠ | ቢ | ቡ | ሰ | ለ | ሞ | ን |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- ቤተ ክርስቲያን ሦስት ክፍሎች አሏት፤ እነሱም ቅድስት፣ መቅደስና ቅኔ ማኅሌት ናቸው።
- ቅኔ ማኅሌት ፡- ካህናት፣ ደባትራን ፣ መዘምራን ስብሐተ እግዚአብሔር የሚያደርሱበት ፣ መዝሙር የሚዘምሩበት ክፍል ነው።
- ቅድስት ፡- ቆራብያን ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉበት፣ ሥርዓተ ተክሊል የሚደርስበት ክፍል ነው።
- መቅደስ ፡- የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚቀመጥበት ፣ሥልጣነ ክህነት ብቻ ያላቸው የሚገቡበት ፣ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የሚፈተትበት ክፍል ነው።

## የማጠቃለያ መልመጃ

### ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።

፩. መዘምራን ስብሐተ እግዚአብሔር የሚያደርሱበት ስፍራ ምን ይባላል?

፪. የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚቀመጥበት ስፍራ ምን ይባላል?

፫. የሚቆርቡ ምእመናን ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉበት ስፍራ ምን ይባላል?